የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ / 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጽ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ጽ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በጽ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፤

የጽ/ቤቱን የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ወጪ**

1. ከጽ/ቤቱ ዋና ኃላፊ ብር 1,974.72 እንዲሁም ከምክትል የጽ/ቤት ኃላፊ ብር 1,907.64 በድምሩ ብር 3,882.36 ከደሞዛቸው ያልተቀነሰ የህክምና መዋጮ ተገኝቷል፡፡

2. ጽ/ቤቱ ለፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን መክፈል የነበረበትን የቤት ኪራይ በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት የቤት ኪራይ ቅጣት በሚል ብር 9,029.20 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል::

3. የግዥ ዕቅድ ውስጥ ሳይካተቱ የተለያዩ ግዥዎች ተፈጽሞ በድምሩ ብር 370,377.54 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

ከላይ ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሣያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች**

4. ለደመወዝ ዝግጅት ሠራተኞች በሥራ ላይ መኖራቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ለፋይናንስ ሳይቀርብ ደመወዝ የሚዘጋጅ መሆኑ ታውቋል፡፡

5. ለጽ/ቤቱ ከተመደበው ጠቅላላ በጀት ብር 4,215,046.74 ስራ ላይ ያልዋለ (25.50%) ተገኝቷል፡፡

6. አለአግባብ የሠራተኛ ዝውውር ተፈጽሞ መገኘቱ፤

ከሠላምታ ጋር

አንድነት ብዙሰው
የኦዲት ሥራ አስኪያጅ
ቀን 15/4/2012